**ሰላም ለደብተራው!**

ከመብረቁ ዘቋራ (ለደብተራው ቀንና ለደብተራው ድረ-ገጽ 2ኛ አመት የተጻፈ፣ ህዳር 28፣ 2000 ዓ. ም.)

እንኳን ለደብተራው፣ ድረ-ገጽ መጽሔት፣
ለተሳሰብንበት፣ ሁለተኛው ዓመት፣
አምላክ አደረሰን፣ የትም ባለንበት!!

ሰላም! ሰላም! ወልደ ገብረ-መድኅን ደብተራው፣
በፍጽም አልጠግበውም፣ ስምህን ደጋግሜ ስጠራው፣
ጸገየም አሉህ አበበ፣ ሁሉም ያንተ ድባብ ነው፣
የትግልም ሆነ የሙያ፣ የሊቅነትህ ዓርማው፣
ተሰምቶ አይጠገብም፣ የማያልቅብህ ቅኔው።

ጸገየ ደብተራው፣ ደብተራው አበበ፣
በሃሳብ እያየሁ፣ ዓይኔ አንተን ተራበ።
ሁኔታህን አውቆ፣ መቼ በጠገበ?
ደብተራው ጠራቢው፣ አቤ ኮሚሳሩ፣
ደብተራው ቀስቃሹ፣ ጸገየ መምህሩ፣
ጸገየ አይታክቴ፣ ቆራጡ ደፋሩ፣
አንተን ወርቃችንን፣ ጌጣችን ይሠሩ!
ምርጥ ዕቃ መሆንክን፣ ሳያውቁ ከቀሩ፣
በትግል ገበያ፣ ምንኛ ይከሥሩ!?

ወያኔ ደፋር ነው፣ የሌለው ይሉኝታ፣
ጠይቅ ይልህ ይሆን፣ አንተንም ይቅርታ?
ምን ስቃይ ቢበዛ፣ ግፍ ባይመረጥም፣
የወያኔ እስር ቤት፣ አንተን አይለውጥም!!
ደብተራው በርካሽ፣ ራሱን አይሸጥም።
የማይላላው ትጥቅህ፣ የቅኔ ዝናርህ፣
አልጠራጠርም፣ አይደንዝም ጦርህ።
ምንጊዜም አይላላም፣ ኢሕአፓ ማተብህ!!

ካንተ ተለይቼ፣ ብዙ ከማመካኝ፣
ምነው ካንተ ጋራ፣ ወያኔ በበላኝ?!
የከተማው ትግል፣ ምንም አልተመቸኝ።

ጥራኝ አባቆራጥ! ጥራኝ ኮሚሳሩ!
ለአንተም ይሻልሃል፣ ብቻ ከማደሩ!!!

ደብተራው! ደብተራው! ደብተራው ቢሷችሁ፣
ከትግል የሸሸ፣ ባንዳ አይምሰላችሁ።
ደብተራው! ደብተራው! ደብተራው ቢሷችሁ፣
ተራ፣ ጥራዝ ነጠቅ፣ ባዶ አይምሰላችሁ።

ደብተራ ተብሎ፣ ኮርቶ ለመጠራት፣
ሁለ-ገብ ሁኖ፣ ትጥቅን በማሟላት፣
ተጠያቂ ሆኖ፣ ተሟልቶ መገኘት።
የመጣው ቢመጣ፣ ቢነጋም ቢመሽም፣
ደብተራው ጊዜ አይቶ፣ ከትግል አይሸሽም።
ለሚያስሮጠው ሁሉ፣ ፍርሃት ለበዛበት፣
ደብተራው ሐኪም ነው፣ የትቅማጥ መድኃኒት።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ቁርጥማታም ሁሉ፣ የሸሸ ከትግል፣
የደብተራውን ስም፣ ማጥፋት ይከጅላል።

የተስተካከለ፣ ሙያው የሚያረካ፣
ደብተራው ሚዛን ነው፣ ሙያን የሚለካ፣
ደብተራው ሚዛን ነው፣ ዕብለት የሌለበት፣
ሁሉም በየፈርጁ፣ የሚመዘንበት፣
የሁሉም መማሪያ፣ ድረ-ገጽ መጽሔት።

ደብተራው በጥራት፣ የወርቅ ሚዛን ነው፣
ቢቀበር ቢሸሸግ፣ ዝገት የማይበላው።
አንት የትግራይ መሬት፣ ብዙ ቅርስ የባለህ፣
ደብተራው ወርቅ ነው፣ ጨርቅ እንዳይመስልህ።

እንዳልባሌ ዕቃ፣ ብትጥሉት የትም፣
የወርቅ ሚዛናችን፣ ደብተራው አይዝግም።
ቢሸሸግም እንኳ፣ የትም ተደብቆ፣
ወርቃችን ደብተራው፣ ይታየናል ደምቆ።

የደብተራን ሥራ፣ ሙያውን ሳታውቁ፣
ደብተራን ለመናቅ፣ አትመጻደቁ!
የደብተራ ሙያ፣ ረቂቅ ነው ዚቁ፣
ደብተራ አይተችም፣ ጥራዝ በነጠቁ!

መሪዎች ሲያዛቡ፣ ፍትሕና ብያኔ፣
ደብተራው አይምርም፣ ይጠርባል በቅኔ።
ለሻገተ መንግስት፣ ጊዜው ላለፈበት፣
ደብተራው ይግታል፣ የቅኔ መዲኃኒት፣
የማወራረጃ፣ አክሎ ጥይት።

«ቁማር ጨዋታ ተጫውቼ፣
ገንዘቤን ሁሉ ተበልቼ፣
ምንኛ ዕድሌ ባማረ፣
ዘውዱን ገልብጨው በነበረ!!!»
ይል ነበር ደብተራው፣ በቅኔ ፈጠራ፣
ግርማዊውን ንጉሥ፣ በፍጹም ሳይፈራ።
ደግሞም ስልጣን ሲይዝ፣ ኋላ ወታደሩ፣
ሳያንገፈግፈው፣ የትግሉ መምረሩ፣
«ይጠራሃል ደኑ፣ ይጠቅስሃል ዱሩ፣
ከመሸገበቱ፣ ያባትህ ጀግንነት፣ ኩራትና ክብሩ፣
አያመሻሹበት፣ አያድሩበት ቦታ፣
የፋሽስት እንግዳ፣ መቼ አለው ይሉኝታ!»
እያለ በቅኔም፣ ያርስ ነበር ጠምዶ፣
ተግባርን ከሀሳብ፣ አስማምመቶ፣ አዋህዶ!

ደብተራ! ደብተራ! ደብተራ! ደብተራ!
ባለህበት ቦታ፣ ብርሃንህ ይብራ፣
በኢሕአፓነትህ፣ ተከታይህ ይኩራ!
እግዜር ይሠውርህ፣ ከክፉ መከራ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com